Australian Government

Department of Immigration and Citizenship







# እንግሊዝኛ እንዲማሩ ልንረዳዎ እንችላለን

## የጎልማሳ መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም

### ለምድ ነው እንግሊዝኛ መማር ያለብኝ?

አሁን አውስትራሊያ ውስጥ ስለሆኑ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማሩ ጠቃሚ ነው።

እንግሊዝኛ የአውስትራሊያ ብሄራዊ ቋንቋ ነው። በአውስትራሊያ ውስጥ ሰዎች ብዙ ቋንቋዎችን ይናገራሉ፣ ነገር ግን በአውስትራሊያ ውስጥ አብሮ ለመኖር እንግሊዝኛ መናገርና መረዳት ይኖርብዎታል። ያለ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሥራ ለማግኘትና እራስን ችሎ ለመኖር ያስቸግራል። እንዲሁም የአውስትራሊያ ዜግነትን ለማግኘት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ያስፈልግዎታል።

### የጎልማሳ መጤ እንግሊዝኛ ፕሮግራም ምንድ ነው?

ይህ ፕሮግራም AMEP ተብሎ ሲጠራ ለሚፈቀድላቸው ጎልማሳ መጤዎች እና በአውስትራሊያ ውስጥ መሰረታዊ የሆኑ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ይሰጣል።

የ AMEP ከእንግሊዝኛ በላይ ያስተምራል። እንዲሁም ስለ አውስትራሊያ ሕብረተሰብ፣ ባህልና ልምዶች ይማራሉ። ከርስዎ ጋር ተመሳሳይ ልምድና ዓላማ ያላቸውን ሌላ በቅርቡ የደረሱትን መጤዎች በማግኘት ብዙ አዳዲስ ጓደኞችን ለማፍራት ይችላሉ።

AMEP በአውስትራሊያ መንግሥት የገንዘብ እርዳታ የሚካሄድ ፕሮግራም ነው።

### ለፕሮግራሙ ይፈቀድልኛልን?

በአውስትራሊያ ውስጥ ሰፋሪ መጤ ማይግራንት ወይም ስደተኛ ከሆኑና የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ቪዛ ካገኙ ታዲያ እንግሊዝኛ ትንሽ የሚያውቁ ወይም የማይናገሩ ከሆነ ይህ ፕሮግራም ሊፈቀድልዎ ይችላል። የጊዚያዊ ቪዛ ላላቸው አንዳንድ መጤዎች በዚህ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ሲችሉ እንዲሁም እድሚያቸው ከ15 ዓመት እስከ 17 ዓመት ለሆኑ አንዳንድ ወጣቶች በዚህ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ይችሉ ይሆናል።

አውስትራሊያ ውስጥ እንደደረሱ ወይም የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ እንዳገኙ በስድስት ወራት ውስጥ በአንደኛው የ AMEP አገልግሎት አቅራቢ መመዝገብ ይኖርብዎታል። በአንድ ዓመት ውስጥ የእንግሊዝኛ ክፍለ ትምህርት መጀመር አለብዎ።

የቪዛ ቀን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ወይም ለሥራ የሚሆን እንግሊዝኛ እስከሚችሉበት ጊዜ (ቀድሞ ለደረሰው) ለአምስት ዓመታት የ510 ሰዓታት የእንግሊዝኛ ኮርሶች በ AMEP ፕሮግራም አማካኝነት እንግሊዝኛ መማር ይችላሉ።

ቅድመ ስደት ባጋጠምዎ ችግር ምክንያት (ለምሳሌ ስቃይና በደል) ወይም ባለዎት ውሱን የትምህርት እድል ሳቢያ ለየት ያለ ፍላጎት ካስፈለግዎ ተጨማሪ ትምህርት እንዲሰጥዎ ይፈቀድ ይሆናል።

እንዲሁም ለሥራና ስልጠና (SLPET) ፕሮግራም በቋንቋ የማረጋጊያ መሸጋገሪያ አማካኝነት ተጨማሪ የማስተማር አቅርቦት ይሰጣል። በአውስትራሊያ የሥራ ቦታ ባህልና ልምዶች እስከሚያገኙ ድረስ በተለይ ለሥራ የሚሆን እንግሊዝኛ ለመማር ይህ SLPET ለደንበኞችና ለሥራ ያተኮሩ ኮርስ በመስጠት ይረዳል።

### ፕሮግራሙ ምን ያህል ያስከፍላል?

በፕሮግራሙ በኩል መማር እንዲችሉ ለተፈቀደላቸው አብዛኛዎቹ አይከፍሉም።

### ማን ነው የሚያስተምረኝ?

የአካባቢ ድርጅቶች፣ አገልግሎት አቅራቢዎች በተባሉት የ AMEP ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ አገልግሎት አቅራቢዎች በእንግሊዝኛ ማስተማር የሰለጠኑና የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ አስተማሪዎችን ይቀጥራሉ።

በፕሮግራሙ መሳተፍ ስለመቻልዎ በአካባቢዎ አገልግሎት አቅራቢ በኩል ይነገርዎታል። እንግሊዝኛ የሚማሩበትን ጥሩ መንገድ ሊመርዎት ይችላሉ።

በቤተሰብ ወይም በሥራ ምክንያት የጀመሩትን ክፍሎች ለማቆም ፍቃድ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

የትኛው ኮርስ ለርስዎ ፍላጎት እንደሚስማማ የርስዎ አገልግሎት አቅራቢ ይመክርዎታል። ይህንን የሚያደርጉት አሁን ባለው ሥራዎና የቤተሰብ ሁኔታ እንዲሁም የእንግሊዝኛ ችሎታዎ መነሻ በማድረግ ይሆናል። እንዲሁም በበለጠ የሚማሩበትን መንገድ ለመርዳት እቅድ ሊያወጡ ይችላሉ።

## እንግሊዝኛ በምማርበት ጊዜ ልጆቸን ማን ያይልኛል?

ወደ ክፍል በሚሄዱበት ጊዜ ለልጅዎ የሀጻን እንክብካቤ መስጫ ያለ ክፍያ በነጻ በርስዎ AMEP አገልግሎት አቅራቢ በኩል ሊቀናጅልዎ ይችላል። ለትምህርት ቤት እድሜ ላልደረሱ ህጻናት ያለ ክፍያ በነጻ ህጻን እንክብካቤ የሚሰጥ እርስዎ ወደ ክፍል በሚሄዱበት ጊዜ ብቻ ነው።

በበለጠ መረጃ ለማግኘት የሀጻን እንክብካቤ እውነታ ወረቀትን ለርስዎ AMEP ማእከል መጠየቅ ነው።

## የት ነው የምማረው?

አገልግሎት አቅራቢዎች በተለያየ ጊዜ (ቀን፣ ምሽትና ቅዳሜና እሁድ) እና በተለያየ ቦታ ማለት ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆችና የማህበረሰብ ማእከላት እንደ ቤተክርስቲያንና መስጊዶች ላይ የሙሉ ቀን እና የትርፍ- ጊዜ ኮርሶችን ያቀርባሉ።

በገጠርና በክልላዊ አካባቢ እንዲሁም በታላላቅ ከተማዎች ላይ በአገልግሎት አቅራቢ በኩል ኮርሶች ይቀርባሉ።

## በክፍሎች ላይ መገኘት ካልቻልኩስ ምን ይደረጋል?

### የርቀት ትምህርት

AMEP የርቀት ትምህርት ፕሮግራም አለው። ስለዚህ ኮርሱ የበለጠ መረጃና ምክር በርስዎ አገልግሎት አቅራቢ በኩል ሊቀርብልዎ ይችላል።

ፕሮግራሙ የሚተላለፈው በኢንተርኔት መስመር ላይ ወይም ተከታታይ በሆነ የጽሁፍና በሚታይ አውድዮ ማስረጃ አማካኝነት ሲሆን ይህም መጽሐፍትንና የሚታይ አውዲዮ ማስረጃዎችን መጠቀም ያካተተ ነው። እንዲሁም በስልክ ከባለሙያ አስተማሪ ጋር ብዙጊዜ ግንኙነት ይኖርዎታል። በኮርሱ ላይ በሳምንት ቢያንስ አምስት ሰዓት ማጥፋት ይኖርብዎታል።

ራዲዮ ማዳመጥ፣ ጋዜጣንና ማስታወቂያዎችን ማንበብ፣ ስለ ራስዎ መናገር፣ መረጃን መጠየቅ፣ ቅጾችን መሙላትና ደብዳቤዎችን መጻፍ በዚህ እንቅስቃሴና ተግባር ላይ ይካተታል።

### በቤት ውስጥ አስተማሪ አሰራር

AMEP ፕሮግራም ለማግኘት የሚፈቀድልዎ ከሆነና በክፍሎች ላይ መምጣት የማይችሉ ከሆነ ከቤት ውስጥ አስተማሪ ጋር ለመሥራት ይፈቀድልዎ ይሆናል።

እንግሊዝኛ ለመማር ጥሩ መንገድና በአውስትራሊያ ውስጥ ስለ ቀን ተቀን ኑሮ እንዲረዳዎ ከቤት ውስጥ አስተማሪዎ ጋር በመወያየት ይረዳዎታል።

በዚህ አሰራር ዘይቤ የርስዎ AMEP አገልግሎት አቅራቢ የበለጠ መረጃና ምክር ሊሰጥዎ ይችላል።

## የ AMEP ክፍሎችን ከመጀመር በፊት

AMEP ክፍሎች ከመጀመርዎ በፊት ከርስዎ AMEP ማእከል ጋር ለመገናኘት ቀጠሮ ማቀናጀት ያስፈልግዎታል ይህም:

- የእንግሊዝኛ ደረጃዎን ለመገምገም
- በየሳምንቱ የሚማሩበትን ሰዓታት ቁጥርና የሚሄዱበትን ክፍል ዓይነት ለመስማማት
- ስለ ህጻን እንክብካቤ መስጫ ማስፈለጉንና ምን ዓይነት የ AMEP ማእከል ሊረዳዎ እንደሚችል ለመወያየት
- ለርስዎ ትምህርትና የሥራ ዓላማዎች ሊበጅ የሚችል ግላዊ መሸጋገሪያ መመሪያ ማውጣት እንዲሁም ምን ማድረግ እንዳለብዎትና እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ መማር። ዓላማዎን ወደ ግብ ለማድረስ የደረሱበት መሻሻል እንግሊዝኛ በበለጠ በሚማሩበት ጊዜ በርስዎ እቅድ ላይ ይመዘገባል።

## ለበለጠ መረጃ

የበለጠ መረጃ ለማግኘት ለኢሚግሬሽንና ዜግነት መምሪያ ጥያቄ ማቅረቢያ መስመር በቁጥር 131 881 (በአውስትራሊያ ውስጥ ማንኛውም ቦታ ሆኖ በአካባቢ ጥሪ ሂሳብ) መደወል ይችላሉ።

ስለ AMEP መረጃ ለማግኘት ማለት ለርስዎ ቅርበት ያለው አገልግሎት አቅራቢ በድረገጽ፣ www.immi.gov.au/amep ማግኘት ይቻላል።

የማስተርጎም እርዳታ ከፈለጉ ለትርጉምና አስተርጓሚ አገልግሎት (TIS) National በስልክ 131 450 (በአውስትራሊያ ውስጥ ማንኛውም ቦታ ሆኖ በአካባቢ ጥሪ ሂሳብ) መደወል ይችላሉ። የትርጉምና ማስተርጎም አገልግሎት በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ግልጋሎት ይሰጣሉ።